# <u>እንኳን ደስ አላችሁ !</u>

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት መቋቋሙን ከአበሰራችሁ በኋላ ይህንን የመጀመሪያውን ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ታላቅ ጉባዔ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆናችሁን ስሰማ፣ የተሰማኝ ደስታ ከፍተኛ ነው። የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት መቋቋም ዋና ዓላማ፣ ሴቶች የህብረተሰቡ የጀርባ አጥንትና፣ የህብረተሰቡም ግማሽ አካል ሆነው እያለ ሴቶችን ያላሳተፈ ወይም ያላካተተ ትግል ሆነ እንቅስቃሴ እክል የሚያጋጥመው መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በመክተት ይህንን ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት መመስረታችሁ ታላቅ እርምጃ ነው። በዓለም ላይ የሚታየው የሰብዓዊ መብት መጣስ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የሰላም መደፍረስና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚታየው የሰው ልጅ ፍልሰት በሙሉ፣ ከሁሉም በላይ የሚነካቸውና የሚሸከሙት ሴቶችና ልጆች ናቸው።

ሴቶች የህብረተሰብ ግማሽ አካልና የጀርባ አጥንት ናቸው ሲባል የተሸከሙት ሃላፊነት <u>ልጅ ከመውለድ ጀምሮ ህብረተሰብንም እስከ መቅረፅ ድረስ</u> ነውና፣ ሚናቸው/ድርሻቸው ከፍተኛ መሆኑ አያጠያይቅም። ለዚህም ነው ያለሴቶች ተሳትፎ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ለውጤት ወይም ለግብ አይበቃም የሚባለው።

ሴቶች ሕብረተሰብን የሚቀርፁ በመሆናቸው የሴቶችን እንክብካቤና ድጋፍ፣ የሴቶችን ትብብርና ተሳትፎ፤ እንዲሁም የሴቶችን እምቅ ኃይል ያልጨመረና ያላካተተ እንቅስቃሴ ምንጊዜም ቢሆን አንድ እርምጃ ወደፊት ሁለት እርምጃ ግን ወደ ኋላ የቀረ ነው።

ሴቶች የህብረተሰብ ግማሽ አካል ናቸው ሲባል ከሁሉ በፊት ቀዳሚ ሚናቸው ህብረተሰብን መቅረፅ በመሆኑ መጀመሪያ አንድ ህገር እንደ ሃገር፣ አንድ ህብረተሰብ እንደ ህብረተሰብ ለመቆም፣ የሴቶችን ተሳትፎና ሚና ግዴታ ማካተት ይኖርበታል። ሴቶችን ያልጨመረ ወይም ያላካተተ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንደመጓዝ ይቆጠራል። ሴቶችን ያላሳተፈ እድገት፣ ሊኖር አይችልም። ሴቶችን ያላሳተፈ ልማት፣ ፈፅሞ ማሰብ አይቻልም። ሴቶችን ያላሳተፈ ሥልጣኔ፣ ሥልጣኔ ሳይሆን ኋላቀርነት ነው። ሴቶችን ያላሳተፈ

ፖለቲካ የተጨናገፈ ነው። በአጠቃላይ ሴቶችን ማገርና ምሰሶ ያላደረገ ሀገር እንደ ሃገር መቆም አይችልም።

በመሆኑም ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት፣ በዓለም ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሴቶችን በአንድ ላይ በማያያዝ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የዴሞክራሲ አለመከበር፣ የሰብዓዊ መብት መጣስ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት ለማስቆም በሚደረገው ያላሰለሰ ትግል ከወንድሞቻችን ጎን ለጎን እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንቀጥል ያስችለን ዘንድ፣ አበረታች ጅምር ነው። ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት መመስረቱ ቢዘገይም ግን አሁንም መቋቋሙ ጎሽ የሚያሰኝ ነው። በዚህ አጋጣሚ በዓለም ላይ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን እናቶችና እህቶች በሙሉ በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

አያልነሽ